# የስድስተኛ ክፍል አማርኛ የሞዴል ፈተና መለማመጃ

## ጥያቄ ሶስት

1. ሰውነታቸው **ኮስመን** ያለ ነው ፡፡ ለተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ

   ሀ) ጠንከር ለ) ጎስቆል ሐ) ወፈር መ) ደንደን

2. የነፍስ ወከፍ የሚለው ሃረግ የሚያስተላልፈው መል ዕክት

   ሀ) ለጋራ ለ) ለእያንዳንዱ ሐ) ለነፍስ ማዳን መ) ለፅድቅ

3. ከሚከተሉት ውስጥ የተፀውዖ ስም የትኛው ነው ?

   ሀ) ወንድ ለ) አባት ሐ) ላም መ) ሰናይት

ይችን ማጭዴን ሆዷን አሚታል፣

እየቆረጠ ያጋድማታል፣

4. ይህ ግጥም የሚዜመው ለምንድን ነው ?

   ሀ) ለውቂያ ጊዜ ለ) የአጨዳ ግጥም ሐ) ፍከራ ግጥም መ) የ ቀረርቶ ግጥም

5. በቆሎው እንጭጭ ስለሆነ ሲበሉት ይጣፍጣል ፡፡

   ሀ) አሸት ለ) ብዙ ሐ) ለጋ መ) አጭር

6. በስራ ግሎ ለመነሳት የሰው ልጅ **ቆሰቋሽ** ይፈልጋል፡፡

   ሀ) ተንኳሽ ለ) ቀስቃሽ ሐ) ጎትጓች መ) ለ ርና ሐ

7. የዋጋ **ግሽበት** ባለበት ሁኔታ ኑሮን መቋቋም እጅግ ከባድ ነው ፡፡

   ሀ) ግስጋሴ ለ) ንረት ሐ) ፍጥነት መ) ሀ እና ሐ

8. የላም ልጅ እንደተወለደች ምን ትባላለች?

   ሀ) ግልገል ለ) ጥጃ ሐ) ጊደር መ) እንቦሳ

9. ያልወለደች ላም ምን ተብላ ትጠራለች?

   ሀ) ወይፈን ለ) ጊደር ሐ) ጥጃ መ) በሬ

LIVEWORKSHEETS

10. የሌሊቱ **ዕልሙት ተገፎ** ብርሃን ሲወጣ ሁሉም ሰው ከመኝታው ተስፋን ይዞ ይነሳል፡፡

ሀ) ጨለማው ተወግዶ　　ለ) ጨለማው ተተክቶ

ሐ) ብርሃን አስወግዶ　　መ) ምሽትን ቀይሮ

11. ሙዚቀኛው በራሱ **ቅኝት** የራሱን ቅላጼ በመፍጠር ሙዚቃ አወጣ

ሀ) ድምጽ　　ለ) እንጉርጉሮ

ሐ) ሙሾ　　መ) የዜማ ዓይነት

12. የሰዎችን ውስጣዊ ስሜቶች ድብቅ በሆነ ፍቺ መልዕክትን የሚያስተላልፍ የንግግር ዓይነት?

ሀ) ምሳሌያዊ አነጋገር　　ለ) ፈሊጣዊ ንግግር

ሐ) ተረትና ምሳሌ　　መ) ቃላዊ ግጥም

13. በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የሌሎች ሰዎችን ንግግር በራሳችን ጽሁፍ ውስጥ መዋሳችንን ወይም መጠቀማችንን የምንገልጽበት ስርዓተ ነጥብ የትኛው ነው?

ሀ) ..............　　ለ) ()　　ሐ) <<　　>>

መ) !　　ሠ) ፣

14. **"ዓባይ"** የሚለው ቃል ላልቶ ሲነበብ የሚሰጠው ትርጉም ?

ሀ) የወንዝ ስም　　ለ) ሃቀኛ

ሐ) ቃሉን የማይጠብቅ　　መ) የተፀዎዖ ስም

ሠ) የወል ስም

15. **"ልጆቻቸውን"** የሚለው ቃል በም ዕላድ ተነጣጥሎ ሲፃፍ

ሀ) ልጆ-አቸውን　　ለ) ልጅ -አቸው- ን

ሐ) ልጅ-ኦች-አቸውን　　መ) ልጆች- አቸውን

16. ልጁ የተዋሰውን መጽሃፍ **ባለፈው ሳምንት** መለሰ፡፡ ይህ ዐረፍተ ነገር በየትኛው ጊዜ ነው ተተገለፀው?

ሀ) በአሁን ጊዜ　　ለ) በሃላፊ ጊዜ

ሐ) በትንቢት ጊዜ　　መ) በወደፊት ጊዜ

LIVEWORKSHEETS

17. ስለመኪና እውቀት **ጉብይቼ** ነበር ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ :

ሀ) ቀስሜ ለ) ሰብስቤ ሐ) ፈልጌ መ) አጠራቅሜ

18. ታሪካዊ ድርጊት የተፈፀሙባቸውን ቦታዎች **በመቆፈር** ሲል የተሰመረበት ቃል ትርጉም

ሀ) በመፈለግ ለ) በመጎርጎር ሐ) በመፈልፈል መ) ሁሉም

19. እከል ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሆነው :

ሀ) እድገት ለ) እንቅፋት ሐ) ችግር መ) ለ እና ሐ

20. ሊቃውንት ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሆነው :

ሀ) ምሁራን ለ) ደራሲ ሐ) ተዋናይ መ) ሙዚቀኛ

21. **ማጉላት** ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሆነው :

ሀ) ማውጣት ለ) ማሳደግ ሐ) ማሳነስ መ) ማጥፋት

22. እህቱ በሚለው ቃል ላይ የተጨመረው ም ዕላድ:

ሀ) ቁጥርን ያመለክታል ለ) ፆታን ያመለክታል

ሐ) ንብረትን ያመለክታል መ) መደብን ያመለክታል

23. ጌታቸው ጎበዝ ተማሪ ነበር በሚለው ዓ/ነገር ውስጥ ያለው ጊዜ:-

ሀ) የአሁን ጊዜ ለ) የሃላፊ ጊዜ ሐ) የትንቢት ጊዜ

24. ከሚከተሉት ውስጥ የአሁን ጊዜን የሚያሳየው የቱ ነው ?

ሀ) ይመጣል ለ) እያጠና ነው ሐ) አልቋል መ) አጥንቷል

25. ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ የወደፊት ጊዜን ይገልፃል::

ሀ) ተሰብሯል ለ) ለመምጣት ይፈልጋል ሐ) ተጽፏል መ) እየመጣ ነው

26. **የቀለም ቀንድ** የሚለው አባባል ምንን ይገልፃል?

ሀ) ብዕር ለ) የቀለም ማስቀመጫ ሐ) ጎበዝ መ) የሚያምር

27. **በተመስጦ** ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ፍቺ የሚሆነው :

ሀ) በፅሞና ለ) በትኩረት ሐ) በቀልድ መ) ሀ እና ለ

LIVEWORKSHEETS

28. አለም ብዙ ጊዜ ነገሮችን **በአርምሞ** ታልፋቸዋለች ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ

ሀ) በንቀት　　ለ) በጨዋታ　　ሐ) በዝምታ　　መ) በችኮላ

29. ውሻው **አላፊ አግዳሚውን** ይተናኮላል ሲል የተሰመረበት ቃል ፍቺ፡

ሀ) የማያውቀውን　　ለ) ባጠገቡ የሚያልፈውን ሁሉ

ሐ) የቆመውን　　መ) ሁሉም

30. ከሚከተሉት አማራጮች ለልተውና ጠብቀው ሲነበቡ ትርጉም የሚሰጡት፡

ሀ) ፈራ　　ለ) ቀና　　ሐ) በላ　　መ) ለ እና ሐ

31. **ጎበዞች** የሚለው ቃል ላይ ያለው አብዢ፡

ሀ) ች　　ለ) ኦች　　ሐ) ዞች　　መ) ዎች

32. የድመት ልጅ ምን ትባላለች ?

ሀ) ግልገል　　ለ) ሙጭሊት　　ሐ) ጫጩት　　መ) ጨቅላ

33. አባቴ **መዳፈ ሰፊ** ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

ሀ) እጁ ትልቅ ነው　　ለ) ደግ ነው　　ሐ) ቸር ነው　　መ) ለ እና ሐ

34. **እየፈጩ ጥሬ** ማለት ምን ማለት ነው ?

ሀ) የማይደቅ　　ለ) ለውጥ የማያመጣ

ሐ) ውፍጮ የማይችለው　　መ) ይማያምር

35. በነፍስ ወከፍ ማለት ምን ማለት ነው?

ሀ) ነፍስ የሌለው　　ለ) በጅምላ　　ሐ) በጥቅል　　መ) ለእያንዳንዱ

LIVEWORKSHEETS